# ከቤትዎ ጋር የተገናኙትን የሊድ ፓይፖች መተካት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሃብት ይወቁ።


ከከተማው የውሃ ማቅረቢያ እስከ ቤታቸው ድረስ የሚያገናኙት በግል መኖሪያ ቦታ ያሉትን የሊድ ፓይፖች ለመተካት፣ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታን ከእኛ—የዲሲ መንግስት— መጠቀም ይችላሉ። ገቢዎ ምንም ይሁን ምን፣ በሚተኩት ላይ የ 50% ቅናሽ (እስከ $2,500) ያገኛሉ። የቤተሰብዎ ገቢ ከፕሮግራም ገደቦቹ እኩል ወይም በታች ከሆነ፣ ምትኩን በነጻ ወይም በ 80% ቅናሽ ሊያገኙ ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም የሊድ ፓይፕ መተካት የእርዳታ ፕሮግራም (Lead Pipe Replacement Assistance Program) ይባላል እና የቀረበውም የሃይል እና አካባቢ ዲፓርትመንት (Department of Energy and Environment) ከ DC Water ጋር በጋራ በመተባበር ነው።

## ብቁ መሆንዎትን ያረጋግጡ።

እነዚህ **ሁሉ** መግለጫዎች እውነት ከሆኑ፣ እርስዎ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡

- የሚኖሩበት ቤት የራስዎ ነው።
- ቤትዎ የሚገኘው ዲሲ ውስጥ ነው።
- ከከተማው የውሃ ማቅረቢያ እስከ ቤትዎ ድረስ የሚያገናኘው ፓይፕ ከፊሉ ሊድ ነው፣ ይህም ማለት በህዝባዊ ስፍራዎች ያለው ክፍል ሊድ አይደለም ነገር ግን የግል ንብረት ጋር ያለው ክፍል ሊድ ነው። ለቤትዎ ይህ እውነት መሆኑን ለማወቅ “ያመልከቱ” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ እንዲሁም ፓይፖችዎ ሙሉ በሙሉ ሊድ ከሆነ፣ እንዴት ብለው እንደሚተኩ ይማሩ።



ለፕሮግራሙ ተቀባይነት ያገኘ እያንዳንዱ ሰው ቢያንስ 50% ቅናሽ (እስከ $2500) ያገኛል። የቤተሰብዎ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ—ታክሶችን ከመክፈልዎ በፊት ያለው ገቢ—ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ከሆነ፣ ምትኩን በነጻ ወይም በ 80% ቅናሽ ማግኘት ይችላሉ። የቤተሰብ ገቢዎን ለማስላት፣ ከእርስዎ ጋር አብረው የሚኖሩ አዋቂዎች ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን ገንዘብ ይደምሩ። ከዚያ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉትን ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ዋስትና፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያ የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | ለ**ነጻ** የፓይፕ መተኪያ ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ | ለፓይፕ መተኪያ የ**80% ቅናሽ** ያለው ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ |
|---|---|---|
| 1 | $67,950 | $84,900 |
| 2 | $77,650 | $97,050 |
| 3 | $87,350 | $109,150 |
| 4 | $97,050 | $121,300 |
| 5 | $104,850 | $121,300 |
| 6 | $112,600 | $121,300 |
| 7 ወይም ከዚያ በላይ | $121,300 | $121,300 |

## ያመልከቱ።

1. ፓይፖችዎ በከፊል ሊድ መሆናቸውን ለማየት፣ በ DC Water ድረ ገጽ ላይ አድራሻዎን ይፈልጉ። ፓይፖች ሶስት ደረጃዎች አሏቸው፤ የማይታወቅ፣ ከፊሉ ሊድ የሆነ ወይም ሁሉም ሊድ የሆነ።

- ፓይፖችዎ ሁኔታ የማይታወቅ ከሆነ፣ ከ DC Water የሊድ ምርመራ መሳሪያን ይጠይቁ።
- ፓይፖችዎ ሙሉ በሙሉ ሊድ ከሆኑ በህዝባዊ ስፍራዎች ያሉት ፓይፖችዎ በነጻ ለመተካት፣ የበነ ፈቃደኛ የምትክ ቅጽን ይሙሉ። በግል ቦታ ላይ ያሉትን ፓይፖች ለመተካት የሚጠይቀውን ወጪ 100% ክፍያ የመክፈል ሃላፊነቱን እርስዎ ይወስዳሉ። DC Water በህዝባዊ ስፍራዎች ላይ ያሉትን እንዲሁም በግል ንብረት ጋር ያሉትን ፓይፖች በአንድ ጊዜ የመተካት መርሃ ግብር ላይ፣ እርስዎን ያነጋግሩዎታል።

2. ከማመልከቻዎ ጋር ለማስገባት የሚከተሉትን ሰነዶች ይሰብስቡ። እንዴት እንደሚያመለክቱ ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ፣ ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ወይም ስካን ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል።
    - ፎቶ ያለባቸው መታወቂያዎችዎ (ልክ እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ)
    - የእርስዎ DC Water ክፍያ መጠየቂያ
    - ቤትዎ የራስዎ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ (ስምዎ በላዩ ላይ የሰፈረበት እንደ ህጋዊ ሰነድ ወይም ሞርጌጅ መግለጫ)
3. ለተጨማሪ የገንዘብ እርዳታ ብቁ መሆንዎን እኛ እንድናረጋግጥልዎ ከፈለጉ፣ የሁሉም የቤተሰቦችዎ አባል በጣም የቅርብ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የታክስ ተመላሾች ያስፈልጉዎታል። ለሁኔታዎ ብቻ ተፈጻሚነት ያለው ሰነድ ያስፈልግዎታል።
4. በኦንላይን ወይም በፖስታ መልእክት ለማመልከት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ይምረጡ፡
    - በኦንላይን ለማመልከት፣ ይህንንማመልከቻ ይሙሉ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ማመልከቻው እንዲሰቅሉ ያስፈልጋል።
    - በኢሜይል ለማመልከት፣ የተሞላውን ማመልከቻ ወደ leadline.replacement@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ኢሜይሉ እንዲያያይዙ ያስፈልጋል።
    - በፖስታ ለማመልከት፣ የእርስዎን የተሞላ ማመልከቻ እና ከዚህ በታች ባለው አድራሻ የሰነዶችዎን ቅጂዎች አትመው ይላኩ። ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ይኖርብዎታል። እባክዎን ዋናውን ሰነዶች አይላኩ።

        Attn: Lead Pipe Replacement Assistance Program
        The Department of Energy & Environment
        1200 First Street NE, 5th Floor, Washington DC 20002

በማንኛውም ሰዓት ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. እኛ—የዲሲ መንግስት—ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዳገኘና ስለሚቀበሉት የገንዘብ ድጋፍ ለማሳወቅ ኢሜይል እናደርግልዎታለን። ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን በተሳካ ሁኔታ የጨረሱ የቧንቧ ሰራተኞችን እንልክልዎታለን።
2. ከዝርዝሩ ውስጥ የተፈቀደለትን የቧንቧ ሰራተኛ ይምረጡ እና ቤትዎ መጥተው ከጎበኙ በኋላ ዋጋ እንዲነግሩዎት መርሃግብር ይያዙ። ለቧንቧ ሰራተኛው ተቀማጭ ገንዘብ አይክፈሉ ወይም የ DC Water የአስገባውን ዋጋ እስከሚቀበሉት ድረስ ስራ እንዲጀምር አያድርጉት።
3. የእርስዎ ቧንቧ ሠራተኛ የሚሰሩበትን ዋጋ ለ DC Water ያስገባሉ።
4. DC Water ዋጋው ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ግምገማ ያደርጋል። ስለ ማመልከቻዎ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እርስዎንና የቧንቧ ሠራተኛውን በቀጥታ ያገኛችኋል።
5. ዋጋውን እንደተቀበልነውና የድጋፉን መጠን የሚያሳይ ደብዳቤ ከእኛ ከተቀበሉ በኋላ **ባሉት 90 ቀናት ውስጥ** ፓይፖችዎን እንዲተካ ከቧንቧ ሠራተኛው ጋር መርሃ ግብር ያወጣሉ።
6. ቧንቧ ሠራተኛዎ ፈቃድ ያገኛል እና ስራ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ 48 ሰአታት በፊት ስለመተካት ስራው ለ DC Water ያሳውቃል።
7. የእርስዎ ፓይፖች ይተካሉ!
8. የቧንቧ ሰራተኛው የመተካቱን ሰነድ ለ DC Water ያስገባል።
9. ፓይፖቹ እንደተተኩ ለማረጋገጥ እና ስራው የደህንነት ደረጃዎች መከተሉን ለማወቅ፣ DC Water የምርመራ መርሃ ግብር ያወጣል። ለፍተሻው እርስዎ በቤትዎ መኖር አለብዎት።
10. የቧንቧ ሰራተኛው ለ DC Water እርስዎ የተፈቀደልዎትን የገንዘብ ድጋፍ መጠን የክፍያ መጠየቂያ ያስገባል።
11. ከፕሮግራሙ ድጋፍ ከተቀበሉ በኋላ እዳ ካለብዎት፣ መክፈል ላለብዎት የገንዘብ መጠን ከቧንቧ ሰራተኛው የክፍያ መጠየቂያ ይቀበላሉ።
12. ለቧንቧ ሰራተኛው የክፍያ መጠየቂያ መጠኑን ይከፍላሉ። DC Water የእርዳታ መጠኑን ይከፍላል።

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ እርስዎን ካስቀመጥን፣ በ 30 ቀናት ውስጥ ኢሜይል በመላክ እናሳውቅዎታለን።

**ብቁ የሆኑ ሁሉም አመልካቾች ፓይፖቻቸውን ለመተካት እርዳታ ያገኛሉ?**

አይ፣ የዚህ ፕሮግራም የገንዘብ እርዳታ መጀመሪያ በመጣ፣ መጀመሪያ በተስተናገደ መሰረት ላይ ነው። ይህ ፕሮግራም የተጀመረው በኦክቶበር 2019 ስለሆነ ምን ያህል ነዋሪዎች እንደሚያመለክቱ ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንደሚቀበሉ እርግጠኞች አይደለንም።

**ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**

እንደ ኦክቶበር 1 2020፣ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ የቧንቧ ሰራተኞች ዝርዝር ውስጥ አንድ የቧንቧ ሰራተኛ እንዲመርጡ ይጠየቃሉ።

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**

መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎ የእኛን የተመጣጣኝነትና ውጤታማነት ቡድንን በ (202) 535-2600 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያገኟቸው ይችላሉ። ወይም በ leadline.replacement@dc.gov ላይ "LPRAP Application Question" በሚል ርዕሰ መስመር በመጠቀም ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

**እኔ ብቁ አይደለሁም፣ ነገር ግን የቤቴን ደህንነት ለመጠበቅ እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**

በእኛ የቤት ደህንነትእናየሊድ ጥበቃ ገጾች ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

**ከዲሲ መንግስት ምላሽ ከመስማቴ በፊት የቧንቧ ሰራተኛው ፓይፑ ላይ መስራት መጀመር ይችላል?**

አይ፣ የፓይፕ መተካት ስራን ለመጀመር፣ እባክዎ ማመልከቻዎ ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ ይጠብቁ። ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ በ 90 ወናት ውስጥ ከስራ ተቋራጭዎ ጋር የስራውን መርሃ ግብር ማውጣት አለብዎት።

**የምኖረው ኮንዶ ወይም ኩፕ (coop) ውስጥ ነው። ብቁ ነኝ?**

ከከተማ ውሃ አቅርቦት ጋር የተገናኘ ከፊል ፓይፕ ያላቸው ብዙዎቹ ቤቶች የነጠላ የቤተሰብ ቤቶች ናቸው፤ ስለዚህ እንደ ኮንዶዎችና ኩፕስ (coops) ያሉ ጥቂት ባለብዙ የቤተሰብ ህንጻዎች ብቁ ናቸው። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ከፊል የሊድ ፓይፕ ካለው፣ ማመልከት ይችላል። ሂደቱ ለኮንዶዎችና ለኩፕስ (coops) በትንሹ ይለያያል ስለዚህ ከመጀመርዎ በፊት፣ የእኛን የተመጣጣኝነትና ውጤታማነት ቡድንን

በ (202) 535-2600 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ያግኙ። ወይም በ leadline.replacement@dc.gov ላይ ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

**ቤተሰቤ ምንም አይነት ገቢ የለውም። ያንን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?**

ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር **ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሰነድ ማስገባት** ይችላሉ፡

- በውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠየገቢ መግለጫ፣
- Department of Employment Services (DOES፣ በቅጥር አገልግሎቶች ክፍል) ድረ ገጽ "ቀሪ ሂሳብዎ" ዜሮ እንደሆነ የሚያሳይ የእርስዎ "ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መገለጫ" ቅጽበታዊ ገጽ እይታ ((ምሳሌውን ይመልከቱ)፣
- ከቀድሞ አሠሪዎ የተጻፈና ከአሁን በኋላ እዛ እንደማይሠሩ የሚገልጽ ደብዳቤ (ከስራ ከለቀቁ ግን እስካሁን ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን በ DOES እያገኙ ካልሆነ)፣ **ወይም**
- ከ District of Columbia Housing Authority (DCHA፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን)) የመጣው ደብዳቤ የሚገልጸው ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ እንደሌለው ነው

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ማርች 2021 ነው።*